ቀስተ ደመና ሬድዩ ትችት

# በወያኔያች ጩቀላ ፕሮፖጋንዳ ታሪካችንን አንጠየፍም

ጥራዝ ነጠቅነታቸውንና ጥልቀት አልባ አስተሳሰባቸውን ለማጋለጥ ሲሆን ትንሽም ሆነ ትልቅ አጋጣሚ እንዳያመልጣቸው የማሉ የሚመስሉት የወያኔ መሪዎች የአጼ ኃይለሥላሴን የቀብር ስነሥርዓት ምክንያት በማድረግ በመንግሥት ደረጃ መግለጫ አውጥተዋል:: በዚህ አስነዋሪና ይሉኝታ ቢስ መግለጫቸው የቀደሙት ንጉሠ የዚያ የኢትዮጵያን ገበሬዎች ይህ ነው ለማይባል ግፍና የኢትዮጵያን ብሄሮች ለአሰቃቂ ጭቆና የዳረገው አስከፊ ፊውዳል ሥርዓት ቁንጮ ስለነበሩ በህዝብና በታሪክ ፊት ተጠያቂ እንደሚሆኑ አውጀዋል:: ነገሩን እንደዚህ አቀለለው እስከዬት ድረስ እንዴትና ለምን በመንግሥት ደረጃ መግለጫ ማውጣት እንዳስፈለጋቸው ባይነገሩንም ይህ የቀብር ስነሥርዓት ተራ የቤተሰብ ጉዳይ ነው በማለትም ሊያጣጥሉትና ሊያናንቁት ሞክረዋል::

ወደዱንም ጠሉንም አጼ ኃይለሥላሴ እጅግ ብዙ በታየበት በሃያኛው ክፍለ ዘመን ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካና ለዓለም ታሪክ ግዙፍ የሆነ ቦታ የሚኖራቸው ግዙፍ የፖለቲካ መሪ ነበሩ:: ከተራ ደጃዝማችነትና አውራጃ ገዥነት እስከ ንጉሠነገሥትነት በሃገራችን የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ከስልሳ አምስት ዓመታት በላይ ተሳትፎ የነበራቸው ሰው ነበሩ:: ከነዚህ ዓመታት ውስጥ አስራ አራት ዓመት በባለሙሉ ሥልጣን አልጋወራሽነት ለአርባ አራት ዓመት ደግሞ በንጉሰነገሥትነት ቢከፋም ቢለማም የኢትዮጵያን እድል በእጃቸው ይዘውና በትከሻቸው ተሸክመው ከግማሽ ክፍለዘመን በላይ ተጉዘዋል::

በነዚህ ከሰስት ትውልድ በላይ ባካተቱ ረዥም ዓመታት ገና ሃያ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው እድሏን ከተረከቧት ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና ታሪክ፣ ከቀደሟቸው የአገዛዝ ባህልና ዘይቤ፣ እጅግ ተለዋዋጭ ከነበረውና ከሁለት የዓለም ጦርነቶች እስከ ቀዝቃዛው ጦርነት ከዘለቀው የዓለም ሁኔታ፣ መላ አፍሪካ በቅኝ ግዛትነት ሲወድቅ ለትናንሽ አገሮች በማይመች የሃይል ሚዛን ኢትዮጵያን ለማትረፍ ከተደረገው ውስብስብ ትግልና ከመሳሰሉት ክስተቶች በቀሰሙት ትምህርትና ባካበቱት ልምድ ለኢትዮጵያ ያላቸውን ራእይ ለመተግበር ከስልሳ ዓመታት በላይ ደክመዋል::

የአጼ ኃይለሥላሴ ራእይ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ራእይ ሆኖ የሚያውቅበት አንድም ወቅት አልነበረም:: በመጀመሪያው የአገዛዝ ዘመናቸው በለውጥ አራማጅነታቸው ምክንያት ስፍር ቁጥር የሌላቸውና ኃያል የሆኑ ኋላ ቀር ኃይሎች ተፋልመዋቸዋል:: በሁለተኛው የአገዛዝ ዘመናቸው ደግሞ የለውጥ እንቅፋት ሆነብን ያለ አዲስ ትውልድ ተቃውሟቸዋል:: ይህ የማይካድ የታሪክ ሃቅ ነው:: ግን ተስማማንበት አልተስማማንበት ለኢትዮጵያ ሳላቸው ራእይ ደክመዋል ፈቀድንም አልፈቀድን በኢትዮጵያም፣ በአፍሪካም በዓለምም የሃያኛው ክፍለዘመን ታሪክ ግዙፍ ቦታ ይኖራቸዋል::

ከዚህ ስንነሳ የወያኔ መሪዎች ጩቀላ መግለጫ እጅግ እንግዳ ነገር የሚሆንብን ንጉሰነገሥቱን የኢትዮጵያን ገበሬዎች ለግፍና ለርሃብ ዳረጉ ብለው የሚወነጅሉት ሰዎች ኃይለሥላሴ ካረፉ ከሩብ ክፍለዘመን በኋላ ወያኔዎች በተከሉት አስከፊ ሥርዓት ምክንያት የኢትዮጵያ ገበሬዎች አሁንም የርሃብና የግፍ ቀንበር ተሸክመው በማየታችን ብቻ አይደለም:: ይህ መግለጫ እንግዳ ነገር የሚሆንብን ንጉሠነገሥቱን ለብሄር ጭቆና ተጠያቂ አድርገው የሚወነጅሉት ጥቂት ጉጠኞች በጨዋውና በኢትዮጵያዊው የትግራይ ህዝብ ስም ለጥቂቶች ጥቅም የቆመ ህዝብን ከህዝብ ለማናከስ ሆን ተብሎ የተዋቀረ ሥርዓት ስር እንድንወድቅ ማድረጋቸውን በመታ

ዘባቸን ብቻ አይደለም:: ይህ መግለጫ እንግዳ ነገር የሚሆንብን ንጉሰነገሥቱን ጥቂቶችን ለምድራዊ ገነት ለማብቃት ሲባል ብዙሃኑን ለምድራዊ ገሃነም ለዳረገ አስነዋሪ ሥርዓት ተጠያቂ የሚያደርጉት ወያኔያች ዛሬ ባለው ለመከበርም ለመደህየትም ወሰን ያለበጀ ዓለም አቀፍ ሥርዓት ውስጥ ሙሰኛና የስድ ገበያ ኢኮኖሚ ተክለው ለጥቂት ህብረብሄር ስግብግቦች ቀጥ ያጣ መከበር ብዙሃኑን ወደ ቀጥ ያጣ ማጣትና መራቆት ይዞ የሚነጉዱ አስነዋሪ ሥርዓት በመትከላቸውም ብቻ አይደለም::

ከወያኔ መሪያች ጨቅላና ጥራዝ ነጠቅ አስተሳሰብ ጋር መሰረታዊ የሆነ የአይታ ልዩነት አለን:: የወያኔን መግለጫ አሳፋሪና አስነዋሪ ሆኖ የምናገኘው እነሱ ከደደቢት ተነስተው አዲስ አበባን ከመቆጣጠራቸው በፊት የነበረው የመቶም ይሁን የሶስት ሺ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ እንዳለ ጨርሶ ፋይዳ ቢስ የሆነ፣ ልንኩራበት ሳይሆን ልናፍርበትና ልንጠየፈው የሚገባ የጽልመት ታሪክ ብቻ እንደሆነ አድርገው ለማቅረብ ያላቸውን አጉል ዝንባሌ የሚያንጸባርቅ መግለጫ ሆኖ ስላገኘነው ነው::

በኛ ግምት ማንም ህዝብ ቢሆን፣ በተለይ ደግሞ እንደኢትዮጵያ ህዝብ በረጅም ጊዜ የውጣ ውረድ ታሪክ ውስጥ ያለፈ ህዝብ ከሆነ ያለፈውን ሁሉ በጽልመት ገጽታው ብቻ ማየት አይችልም:: ይህንን ካደረገ ካለፈው ትምህርት አይቀስምም:: የወደፊቱንም ቢሆን በብሩህ ተስፋ ገጽታው ለማየት ስለሚሳነው ህልምና ራእይ ይዞ ሊታገል፣ ሊሰዋና ድል ሊያደርግ አይቻለውም::

ከዚህም በመነሳት እና ከወያኔ ጉጠኞች ባሻገር ለዚች አገር ህልምና ራእይ አለን የምንል ታጋዮች የአጼ ኃይለሥላሴንም ሆነ በአጠቃላይ ያለፈውን ታሪካችንን በጽልመት ገጽታው ብቻ አናየውም:: ያለፈው ታሪካችን ከሁሉም አንጻር ተመርምሮና ተተንትኖ፣ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ገጽታው ተመዝኖ፣ ለቀጣዩ ኢትዮጵያዊ ራእይና ትግል የሚጠቀመው ተይዞ የሚጣለው ተጥሎ እንዲያገለግል ሆኖ መመርመር አለበት እንላለን:: በመሆኑም ወያኔያች እንደሚሉን ይህ የቀብር ስነሥርዓት ቀን ተራ የቤተሰብ ጉዳይ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ሁሉ የቻሉትን ያህል አጼ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስላላቸው አወንታዊም አሉታዊም ስፍራ አሰላስለው ለመጭው ጊዜ የሚቀስሙትን ትምህርት ለመቅሰም የሚቀርቡበት ቀንና አጋጣሚ መሆን አለበት እንላለን::

በመጨረሻም ንጉሠነገሥቱ በግፍ ተገድለው ወግና ማእረግ ያለው ቀብር ተነፍገው ከተወረወሩበት ጉድጓድ አውጥቶ በክብር እንዲቀበሩ ጥረት ላደረገው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት አድናቆታችንን እየገለጽን በዚች እለት እንኳን ታላቅ የፖለቲካ መሪ ለማስታወስ ለተሰበሰቡት የንጉሳዊ ቤተሰብ አባላት የሃዘናቸው ተካፋይ እንደሆንን ልንገልጽላቸው እንወዳለን::

ቀስተ ደመና ሬድዮ
ጥቅምት 23 ቀን 1993 ዓ.ም.